PDF-XChange
Click to buy NOW!
www.docu-track.com
PDF-XChange
Click to buy NOW!
www.docu-track.com

# አንድ እንበል ጎበዝ

የተከበራችሁ ወገኖቼ ይህችን ጽሁፍ ስጽፍ፡ ኢራን በመካሄድ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ በቴሌቭዥን እየተከታተልኩ ለምን እኛም እንደሌሎቹ ሆ! ብለን አንነሳም? ችግራችን ምንድን ነው? የሚለውን እያሰላሰልኩ ነው።

ለመበደሉ ከሆነ ተረግጠናል፣ተዋርደናል፣ ከሰው በታች ሆነናል መሪዎቻችን (ወያኔ) "ይህንን ሕዝብ መምራት ሳይሆን እንደ ከብት እየነዳነው ነው" እያሉ ይሳለቁብናል። ነገሩን በጥሞና ላየው ሁኔታው ከዛ የተለየ አይደለም፡ በትምህረቱም፣ በንግዱም፣በአስተዳደሩም፣በመከላከያውም መሪዎቹ ጎሳ ላይ መሰረት ያደረገ አሰተዳደር የመሰረቱ ሌላውን ጎሳ እንደባይተዋር የነሱን የተቀማጠለ ኑሮ ተመልካችና አድናቂ ያደረገ ነው።

ይህ ሳያንስ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከ 14 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ረሃብ የሚቆላው አንሶ (በተራ የሚመገበውንና በቀን አንዴ - ሁለቴ የሚበላውን ሳይጨምር) ለአረቦች ለም መሬት መቸብቸብ ጀመሩ፤ተቃወሙን በሚል በየእስር ቤቱ የሚማቅቀውን ቤት ይቁጠረው ፡ እንደ ሙያ አርገው ስርአት ያለበት አገር ለማስመሰል በይስሙላ ፍርድ ቤቶች በወያኔ የተጣፈው ወንጀል ተነቦ፣ በወያኔ በተዘጋጀ ምስክር ተሸሞንሙኖ፡ ለሆዳቸው ባደሩ፡ ለሞያቸው ክብር በሌላቸው ዳኞች ፍርዱ ይነበብና የወያኔ ወንጀል ሕጋዊ ሰውነት ይለብሳል።

ጎበዝ እንግዲህ ይህንን ስርአት ነው ይዘን የምንገኛዋዘው፡ ሰምቶ እንዳልሰማ አይቶ እንዳላየ ለሚሆነው የህብረተሰባችን ክፍል ቀንጠብ ቀንጠብ አድርጌ መረጃዎችን ላቅርብ

- **አገሪቱን ያለ ባህር በር ማስቀረት**; አስፈላጊነቱን ባለማመን ሳይሆን ለተደበቀው ታላቅዋ ትግራይ አላማ ይመቻች ዘንድ ከዛሬው ተቃዋሚያቸው ከቀድሞ ወዳጃቸው ሻቢያ ጋር የተዶለተ ፡(ዛሬ ሻቢያ ነጻ ያወጣችኋል እያሉ ሊመክሩን የሚዳዱም ተቃዋሚ ተባዮች አሉ) በዘመኑ ወያኔ እንደ ጠላት የሚያያቸው ታላቁ ምኒሊክ ከነአሰብ ሌላ ሞት ባይቀድማቸው የዘይላን ወደብ ጭምር ለኢትዮጵያ ለማድረግ ከእንግሊዝ ጋር ድርድር ላይ የነበሩ መሪ ነበሩ።
- **ኢትዮጵያን በዘር መከፋፈል** አንዱን ለሌላው ጠላት አድርጎ ማቅረብ እርስ በርስ ሰዉ ሲባላ እነሱ ሊበሉ፡ ሀሳቡ ከጣሊያን የተወሰደ "ከፋፍለህ ግዛ" አገሪቱም ጎሳ ላይ መሰረት ባደረገ ሁኔታ አማራ ዞን፣ ኦሮሞ ዞን (ኦሮሚያ)...የሚባለው ፈሊጥም ከነሙሶሊኒ የከፋፍለህ ግዛ የተወሰደ እቅድ ነው።
- **ሰራዊቱን ሙሉ እዙን በሚያምኑት በራሳቸው ጎሳ ማዋቀር** በቅርብ በደረሰን መረጃ መሰረት ከ 61 ቁልፍ የእዝ ቦታዎቸ አራቱ በሌላ ጎሳ ሲያዙ የተቀሩት በሙሉ በትግራይ ተወላጆች መያዛቸው፡ ምክንያት ወያኔን በስልጣን ላይ ለማቆት ታማኝነት፡ ሽርተት እንዳይሉ በጥቅም መያዝ  ዛሬ አዲስ አበባ ውስጥ የሰፊ መሬት ባለቤትና የትላልቅ ቤት አከራዮች የወያኔ መኮንኖች ናቸው፡ በሌላ ወገን ኢትዮጵያ የባህር በርዋን እንዳታጣ በየበረሃው የተዋደቁት ጀግኖች ዛሬ በየከተማው እድሜ ለወያኔ ለልመና በቅተዋል፤
- **የኤርትራ መገንጠል** ሳያንስ 1300 ኪሎሜትር ርዝመት 30 ኪሎሜትር ጥልቀት ያለው ቦታ ለሱዳን መስጠት ዓላማው ተቃዋሚ ቡድኖችን መደራጃ ቦታ ማሳጣትና ለወደፊት ታላቅዋ ትግራይ እቅድ  ሊረዱ የሚችሉ ጉዳዮችን ማስተካከል
- **በአሳፋሪ ሁኔታ ሀብት ማግበስበስ** "አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል ይላሉ" ዛሬ የአገሪቱን ሀብት በሙሉ በእጃቸው  ይዘው ኤሌትሪክ በቅጡ ማሰማራት ባልቻሉበት ከተማ ሊፍታቸው የማይሰሩ ፎቆች ሲገነቡ ይታያል፤ በቅርቡ የአቶ መለስ አማካሪ ናቸው እየተባሉ የሚታሙት አቦይ ስብሃት ነጋ የንግድ ድርጅታቸው ኤፈርት ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

PDF-XChange Click to buy NOW! www.docu-track.com

ላይ እየዘረፈ ባከማቸው ሃብት ተወዳዳሪ የሌለውና ንብረትነቱም የትግራይ እንደሆነ ሲናገሩ ሃፍረት እንኳን ፋቸውን ለጎም አያደርገውም።

- በ 2005 ምርጫ የአገሪቱ ፕሬዝዴንት የልጃቸውን ያ 12 ክፍል ማጠናቀቂያ ድግስ በሼራተን ሆቴል እየተዝናኑ፤ የሰጠነው ድምፅ ይከበርልን ያሉትን ዜጎቻችንን በአጋዚ ጦራቸው አስደብድበው ባንክ ሲዘርፉ ተገኝተው ነው አሉ ፡ የነዚህ ንፁሃን ደምም ምንም ካላደረግን ደመከልብ ሆኖ ሊቀር ነው
- በተቃዋሚነት የተደራጁት ወገኖቻችን ከፊሉ **ፓራላማ አዳማቂ** ሆኖ የወከለውን ሕዝብ ሳይሆን ሆዱን የወከለ ሲሆን የተቀረው ደግሞ እርስ በርስ መስማማት አቅቶት ሃይሉን በጋራ ጠላት ወያኔ ላይ ማዋል ሲገባው እርስ በርስ ሲባላ ይታያል።

**ወያኔን ስልጣን ላይ ያቆየው ጥንካሬው ሳይሆን፤ የህዝባችን የሚያምነው ፣ይክደኛል ብሎ የማይፈራው መሪ ማጣት ነው፡** መረጃው ቅንጅትን ደግፎ ሰላማዊ ሰልፍ የወጣውና በጠራራ ጠሀይ የተደበደበው የቅርብ ግዜ መረጃ ነው፡ ለቆሙበት ዓላማ ፍንክች የማይሉ፣ ከግል ስልጣናቸው ይልቅ የአገሪቱን የሕዝቡን ፍላጎት የሚያስቀድሙ ፣ ለሆዳቸው ያላደሩ፥፣የዓለምን የፖለቲካ ሁኔታ ያገናዘቡና በዘረኝነት ያልተለከፉ ከቡድን መብት ይልቅ እምነታቸው በግለሰቦች መብት ላይ የተመረኮዘ መሪዎች ያስፈልጉናል፡ የተቀረነውም ለእያንዳንዱ አቃቂር ከማውጣት፤ ተባብረን ወያኔ ከረጨብን የዘረኝነት አመለካከት ተላቀን፡ ከገባንበት ረመጥ ውስጥ መውጣት መቻል አለብን አለበለዚያ የወያኔ መቀለጃና እትብታችን በተቀበረበት አገር እኩል ዜጋ ሳይሆን ሁለተኛ ዜጋ ሆነን መኖራችን ነው።

የሰማነውን በልቦናችን ያሳድር

ታዛቢው ከሆላንድ